የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ
የፌዴሬሽን ምክር ቤት

The House of Federation
Of
The Federal Democratic Republic
of Ethiopia

ቁጥር 6ጽ-ጣ0/26/5/67
No.
ቀን 26/10/07
Date

ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት

<u>አዲስ አበባ</u>

ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት

<u>ፊንፊኔ</u>

ጉዳዩ፡-<u>የምክርቤቱን ውሳኔ ስለማሳወቅ</u>

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በ4ኛ የፓርላማ ዘመን፣5ኛ ዓመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባው አቶ አልይ ዳዌ ባቀረቡት የሕገመንግስት ትርጉም አቤቱታ መነሻነት ከሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ተመልክቶ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የፌዴሬሽን ምክርቤትን ለማጠናከርና ሥልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 251/1993 ዓ.ም አንቀጽ 11 እና 56 ም/ቤቱ በሕገመንግስት ትርጉም ላይ የሚሰጠው ውሳኔ አጠቃላይ ውጤት እንደሚኖረውና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖችም ውሳኔውን የማክበርና የመፈጸም ግዴታ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት በአቶ አልይ ዳዌ ጉዳይ በየደረጃው በሚገኙ ፍርድቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በምክርቤቱ ታይቶ ሕገመንግስቱን የሚጻረር በመሆኑ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው እና ሕገመንግስታዊ መብታቸው እንዲከበር ሲል ወስኗል፡፡

በመሆኑም በአቶ አልይ ዳዌ የትርጉም ጥያቄ ላይ ም/ቤቱ የሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ 3 ገጽ የተላከላችሁ ስለሆነ በውሳኔው መሰረት እንዲፈጸም እያሳሰብሁ የም/ቤቱ ጽ/ቤትም የውሳኔውን አፈጻጸም ክትትል እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

ከሰላምታ ጋር

ካሣ ተክለብርሃን
የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈ-ጉባኤ

<u>ግልባጭ፡-</u>

ለሕገመንግስትና የክልሎች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ

ለፌዴሬሽን ም/ቤት ጽ/ቤት

<u>በፌዴሬሽን ምክርቤት</u>

ለሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ

<u>አዲስ አበባ</u>

ለአቶ አልይ ዳዌ

<u>ባሉበት</u>

ስልክ 223322 ፋክስ 242304 E-mail: hofethiopia@gmail.com ፖ.ሣ.ቁ. 20212/1000 አዲስ አበባ
Tel. 242303/01 Fax 241208 Web Site: http://www.hofethiopia.gov.et P.O.Box Addis Ababa

# የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት 4ኛ የፓርላማ ዘመን፣5ኛ ዓመት፣2ኛ መደበኛ ስብሰባ

## ሰኔ 18 ቀን 2007 ዓ.ም

አመልካች፡- አቶ አልይ ዳዌ

ተጠሪ፡- አቶ ሙመድ አደም

የኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክርቤት በአመልካች የቀረበውን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገመንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል።

<u>ውሳኔ</u>

የዚህ ክርክር መነሻ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በምዕራብ ሐረርጌ ዞን ሃብሮ ወረዳ ቀበሌ 01 ውስጥ የሚገኝ የእርሻ መሬት ይዞታ ሲሆን በስር የወረዳ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበው የነበሩት የአሁን አመልካች የእርሻ መሬታቸውን ለልጃቸው በኮንትራት ሰጥተውት እየተጠቀሙበት እያለ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ የአሁን ተጠሪ ያለአግባብ መያዙን በመቃወም እንዲያስረክባቸው ክስ መስርተው ነበር።በዚሁ መሰረት ጉዳዩን በቅድሚያ የተመለከተው የሀብሮ ወረዳ ፍርድቤት መሬቱን ልጃቸው ለአሁኑ ተጠሪ እንደሸጠለት ተረጋግጧል በማለት መሬቱን መጠየቅ እንደማይችሉና ሊመለስላቸው እንደማይገባ በመወሰኑ በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ለይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶችም ሆነ ለኦሮሚያና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤቶች ሰበር ሰሚ ችሎቶች ቢያቀርቡም ተቀባይነት በማጣታቸው የፍርድቤቶቹ ውሳኔ በሕገ መንግስቱ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ ስለመሆኑ ጥበቃ የተደረገለትን ድንጋጌ የሚጥስ በመሆኑ ትርጉም እንዲሰጥበት ለአጣሪ ጉባኤው ማቅረባቸውን ምክርቤቱ ተረድቷል።

የፌዴራሉ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤውም የቀረበለትን የሕገመንግስት የትርጉም ጥያቄ ከመረመረ በኂላ አመልካች አቤቱታ ያቀረቡበት የእርሻ መሬታቸው የአሁን አመልካች ልጅ ለነበረው መሀመድ አልይ ለተባለው ሰጥተውት ወደ ሰፈራ ሔዶ በመሞቱ መሬቱ ለሟች ወንድም እንደተላለፈና ይህኛው ልጅ ለተጠሪው እንደሸጠለት ፍርድቤቱ አረጋግጫለሁ



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት

ማለቱንና ይህም ለውሳኔው መሰረት መሆኑን በመረዳት ውሳኔው መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ሀብት መሆኑን ከሚደነግገው የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 40/3/ ጋር የማይጣጣምና የአመልካችን ሕገመንግስታዊ መብት የጣሰ በመሆኑ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል የሚል የውሳኔ ሃሳብ ለምክርቤቱ አቅርቧል፡፡

ከዚህ በመነሳት ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርብ የተመራለት የምክርቤቱ የሕገመንግስት እና የክልሎች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ በሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ እና በምክርቤቱ ባለሙያዎች አስተያየት ላይ ከተወያየ በኃላ ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም ያስፈልገዋል በማለት ምክርቤቱ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሀሳብ አቅርቧል፡፡

ምክርቤቱም አቤቱታውን ከቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ጋር በማጣመር መርምሯል፡፡እንደመረመረውም ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የሃብሮ ወረዳ ፍርድቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው መሬቱ ለአሁን ተጠሪ የተሸጠ መሆኑ ስለተረጋገጠ አመልካች ሊጠይቁ አይችሉም የሚለውን ጭብጥ መሆኑን ምክርቤቱ መረዳት ችሏል፡፡ መሬት ደግሞ በግልጽ የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ሀብት እንደሆነና የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ስለመሆኑ በሕገ መንግስታችን አንቀፅ 40/3/4/ ስር በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ይህንን ሕገመንግስታዊ ድንጋጌ የሚቃረን ማንኛውም ውሳኔ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9/1/ መሠረት ተፈፃሚነት ሊኖረው እንደማይችል የህገመንግስቱን የበላይነት በሚደነግገው እና አንዱ መሰረታዊ መርህ በሆነው ድንጋጌ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

ስለሆነም ፍርድ ቤቶች በግለሰቦች የተፈፀመውን የመሬት ሽያጭ ድርጊት በዝምታ ማለፋቸው ብሎም ያለማረማቸው እንዲሁም ሕገመንግስቱን የማስከበር ኃላፊነት ተሰጥቷቸው እያለ የሕገመንግስቱን ድንጋጌ የሚጥስ ውሳኔ መስጠታቸው ሊታረም የሚገባው በመሆኑ በፍርድቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተፈፃሚነት እንዳይኖረው መደረግ ይኖርበታል፡፡

በመሆኑም ክርክር የተነሳበት የእርሻ መሬት በሽያጭ ከአንዱ ወደ ሌላው ተላልፏል በማለት በሃብሮ ወረዳ ፍርድቤት የተሰጠውና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት እና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጸና የተደረገው ውሳኔ የአመልካችን ሕገመንግስታዊ መብት የጣሰ ስለሆነ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 9/1/ መሰረት ተፈጻሚነት የለውም በማለት ምክርቤቱ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

## <u>ትዕዛዝ</u>

1.በሃብሮ ወረዳ ፍርድቤት የተሰጠውና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድቤት እና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች እንዲጸና የተደረገው እና የአመልካችን ሕገመንግስታዊ የመሬት ባለይዞታነት እና የተጠቃሚነት መብት የሚጻረረው ውሳኔ ተፈጻሚ እንዳይሆን መወሰኑን አውቀው እንዲያስፈጽሙ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት ይተላለፍ።

2.የውሳኔው ግልባጭ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጥ።